'ሴት ልጅ ከርሷ ጋር ባሏ ወይም ዘመዷ ከሌሉ በቀር ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድን አትጓዝ።

ከአቡ ሰዒድ አልኹድሪይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና እንደተላለፈው ‐ ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ጋር አስራ ሁለት ዘመቻዎችን ዘምቷል። ‐ እንዲህ አለ: "አራት ነገሮችን ከነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ሰምቼ አስደንቀውኛል። እንዲህ ብለዋል: 'ሴት ልጅ ከርሷ ጋር ባሏ ወይም ዘመዷ ከሌሉ በቀር ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድን አትጓዝ። ሁለት ቀናት ላይ መፆም የለም፤ ዒደል ፊጥርና አድሓ። ከሱብሒ በኋላ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ሶላት
የለም፤ ከዐስር በኋላም ፀሀይ እስክትገባ ድረስ ሶላት የለም። ወደ ሶስት መስጂዶች ካልሆነ በቀርም ጓዝን ሸክፎ አይኬድም: ወደ
መስጂደል ሐራም፣ ወደ መስጂደል አቅሷና ወደዚህ መስጂዴ።'" [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና) ከአራት ጉዳዮች ከለከሉ። የመጀመሪያው: ሴት ልጅን ያለባሏ ወይም ያለ አንድ ዘመዷ ሁለት ቀን የሚያስኬድ መንገድ ከመጓዝ መከልከል ነው። ዘመዷ የተባሉትም እንደ ልጅ፣ አባት፣ የወንድም ልጅ፣ የእህት ልጅ፣ አጎትና የመሳሰሉት ያሉ ለዘላለም በነርሱ ላይ ለጋብቻ እርም የተደረገችባቸው ቅርብ ዘመዶቿ ናቸው። ሁለተኛው: የዒደል ፊጥርና የዒደል አድሓ ቀንን የመፆም ክልክልነት ነው። በነዚህ ቀናቶች ላይ አንድ ሙስሊም ለስለትም ወይም ለበጎ ፍቃደኝነትም ወይም ለማካካሻ ብሎም መፆሙ ክልክል ነው። ሶስተኛው: ከዐስር ሶላት በኋላ ፀሀይ እስክትገባ ድረስና ጎህ ከቀደደ በኋላ ፀሀይ እስክትወጣ ድረስ ሱና ሶላትን ከመስገድ መከልከሉ ነው። አራተኛው: ከነዚህ ሶስት መስጂዶች በቀር ወደ ማንኛውም ስፍራ ወደርሱ የመጓዝን ብልጫ አስቦ፣ በመጓዝ ምክንያትም ምንዳ ይነባበራል ብሎ በማመን መጓዝ መከልከላቸው ነው። ከነዚህ ሶስት መስጂዶች በቀርም በውስጧ ለመስገድ በሚል ጓዝ ተሸክፎ አይኬድም። ከነዚህ ሶስት መስጊዶች በቀርም ምንዳ አይነባበርም። እነሱም: መስጂደል ሐራም፣ የነቢዩ መስጂድና መስጂደል አቅሷ ናቸው።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/10603